Radio Rainbow
ቀስተ ደመና ሬዲዮ
Radio Arc - En - Ciel

C/o P.O.Box 140 104. 53056 BONN. GERMANY - Fax: (49) 228 / 61 23 81 ~

# ድል በባድመ
## ህዝባዊ ሰልፍ በአዲስ አበባ
## የህወኃት መሪዎች የፖለቲካ ሽንፈት÷የራዕይ ክስረት ሲንጸባረቅ

የካቲት 23 ቀን 1991 ዓ/ም የታላቁን የአደዋ ድል 103ኛ ዓመት አስታኩ ባለፈው ሳምንት በባድመ በእብሪተኛው የሸአብያ ወራሪ ላይ የተመዘገበውን ድል ለማክበር ከአንድ ሚሊዮን ህዝብ በላይ የአዲስ አበባን መንገዶች አስጨናንቆ በመስቀል አደባባይ ድሰታውን ሲገልጽ ውላል::
ሰልፍ በወጣው ህዝብ ብዛት በአዲስ አበባ ታሪክ ውስጥ ይህ ሰልፍ ሁለተኛ ቦታን የሚይዝ ሲሆን በአንደኛ ቦታ የሚቀመጠው የዛሬ 24 ዓመት በዚሁ በየካቲት ወር የኢትዮጵያ ጊዚያዊ ወታደራዊ መንግስት "መሬት ላራሹ" ብሎ ለኢትዮጵያ ገበሬዎች የነጻነት በር ከፍቶ የነበረውን ታላቁን የመሬት አዋጅ ሲያውጅ የተደረገው አድጋፍ ሰልፍ ነበር::

በወቅቱ ሰልፍ የወጣው ቀደም ላሉት አስር ዓመታት ለፍትሃዊ የመሬት ድልድል ከፊውዳሉ መንግሥት ፖሊስና ሠራዊት ጋር እየተናነቀ የተሰዋው ተማሪና ወጣት ብቻ አልነበረም:: ለኢትዮጵያ አዲስ የብርሃን ጮራ መፈንጠቁ የተሰማው የአዲስ አበባ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ሲዘምር ÷ ሲፈነድቅ የዋለበት ሠልፍ ነበር:: ወጣት ሠልፈኞች ከሠልፉ ተራ እየወጡ ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም አንገት ላይ እየተንጠለጠሉ ሲስሟቸው÷አንዳንዶቹ የደስታ እንባ ሲያነቡ ÷ ሌሎች የጮሁበት ጉሮሮ ሲዘጋ ያንን ግብታዊ የህዝብን መፈንደቅ ያዩ የደርግ መሪዎች ይህንን ሁሉ ያልሆነ ትርጉም ሰጡት:: የህዝብን የልብ ትርታ ሰምተው በወሰዱት ህዝባዊ እርምጃ ባገኙት ድጋፍ ላይ ከመገንባት ይልቅ ለዚህ ድጋፍ ያልሆነ አጊጉል ትርጉም አገኙለት:: በህዝብ ላይ ያሻችሁን እንዳሻችሁ የተባሉ መሰላቸው:: ይህም ከባድ አለመግባባት በጸረ-ህዝብ ጎዳና እንዲጓዙ ÷ በህዝብ ደም እንዲዋጁ አደረጋቸው:: እንደዚያ በደገፋቸው ህዝብም ተተፍተው የመጨረሻ መጨረሻ የሆኑት ለመሆን በቁ::

የወያኔ መንግሥት "ነጻ አውጭ" ነን በሚሉ ድርጅቶች ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ሁኔታ ከሠራዊት ጋር ሳይሆን በሠላማዊ የተቃውሞ ሰልፈኛ ላይ እየተኰሰ የአንድን አገር ዋና ከተማ ለመቆጣጠር የበቃ ኃይል ነው:: ከዚያም ወዲህ ቢሆን በሚለውና በሚያደርገው ሁሉ ከተለያዩና ቁጥራቸው እየጨመረ ከሚሄድ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር እየተጣላ በሚሄዱ የረባ የድጋፍ ሰልፍ በሚሉት ነገር የታደለ አይደለም:: ዛሬም ቢሆን ይህንን ሰልፍ የተሳሳተ ትርጉም መስጠት ለወያኔ መሪዎች አደገኛ ሊሆን ይችላል:: እነሱ ባመጡብን ጣጣ ÷ እነሱ ባስታጠቁብን ኃይል ÷ እነሱ ባጎለበቱት እብሪት ሃገራችን ተወራ የኢትዮጵያ ህዝብ በደርዘን ሺ የሚቆጠሩ ልጆቹን ሰውቶ ሃገሩን በማዳኑ የተሰማውን ደስታ ÷ ልጆቹ በባድመ ተራሮች ለከፈሉት መስዋዕትነት ያለውን አክብሮት ለመግለጽ ሰልፍ ወጥቶ ውሏል::

የዚህ ሰልፍ መልዕክት እንደ ዛሬ 24 ዓመቱ ሰልፍ የህዝብን የልብ ትርታ ሰምታችሁ በወሰዳችሁት ርምጃ አበጃችሁ ለወደፊትም ቀጥሉበት የሚል የድጋፍና የማበረታቻ መልዕክት አይደለም:: ለወያኔ መሪዎች የተላለፈው መልእክት በባድመ የተከፈለው ከባድ መስዋዕትነት ትርጉም ይግባችሁ ÷ የኛን ምሳሌ አይታችሁ ከስህተታችሁ ታረሙ ÷ የኛን ድምጽ ሰምታችሁ አቅጣጫችሁን ለውጡ የሚል መልዕክት ነው:: የህወኃት/ኢህአዴግ መሪዎች ይህንን በጎ አቅጣጫ ለመያዝ ከፈለጉ ደግሞ ከሁሉ በፊት የባድመም ድል ሆነ የመስቀል አደባባዩ ሰልፍ የፖለቲካ ሽንፈታቸውንና የራዕይ ክስረታቸውን ያጋለጡ ክስተቶች መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርባቸዋል::

ትላንትና አክሱም የኛ ብቻ እንጂ ለአንተ ምንህ ነው ያሉት ህዝብ ቤት ንብረቱን ርግፍ አድርጎ ትቶ ሺ ኪሎሜትር ተጉዞ የባድመና ሽራሮ ጉዳይ እኔንም ያገባኛል ብሎ የጥይት እራት ሲሆን ÷ ትላንትና ባንዲራህ ጨርቅ ነው ሲሉት የነበረው ህዝብ ዛሬ ይህቺ ለኢትዮጵያችን ሞገስ የሆንችው ክቡር ነገር እንደተከበረች ለትውልድ ታልፍ ዘንድ በደርዘን የሚቆጠሩ ልጆቹን ሲሰዋ ÷ ትላንት ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር የለችም እያሉ ስያቀረሹበት የታዘበ ህዝብ የሚዋደቅላትና ህይወትን የመሰለ ክቡር ነገር የሚሰውላት ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር አለችን እያለ ደሙን ሲያፈስ ÷ ትላንት እንደ እንጀራ ልጅ እየቆጠሩ ያስቃዩት ዜጋ ከነሱ አላፊ ጠፊ ከሆኑት ጥቂቶች በደል ባሻገር በትግራይ ወንድም ህዝብ ላይ የመጣ በዓይኔ የመጣ ነው ብሎ የልጆቹን ደም ከትግራይ ልጆች ደም ጋር ሲያቀላቅል ይህ ሁሉ ከፖለቲካ ሽንፈታቸውና ከራዕይ ክስረታቸው ጋር ምንም ግንኙነት የሌላው ከመሰላቸው የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ዛሬም ብቻ ሳይሆን እስከወዲያኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ህልሙም ሆነ ራዕዩ ÷ ጉጉቱም ሆነ የልብ ትርታው የሚገባቸው አይሆኑም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ ይቻላል::

የወያኔ መሪዎች በኢትዮጵያዊነቱና በሃገር ፍቅር ስሜቱ የቀደማቸውንና ከፊት ሆነው መምራት ያቃታቸውን ህዝብ ከእንግዲህ ከኋላ ኃላ እያሉ መንዳት የማይቻልበት ወቅት ውስጥ እንደገቡ ተገንዝበው በአዲስ ራዕይ አዲስ ፖለቲካ እንዲያራምዱ ይጠበቅባቸዋል:: ሊያፈርሱት የሞከሩትን ኢትዮጵያዊነት ህዘቡ በደሙና በመስዋዕትነቱ መልሶ እየገነባ የለገሳቸውን ትምህርት በጥሞና ማጣጣም ይኖርባቸዋል:: ከዚህ አልፈው ተርፈው ግን እንደ ደርጉ ዘመን ለዚህ መስዋዕትነትና ለዚህ ሰልፍ አጊጉል ትርጉም ከሰጡና ከህዝቡ ጩኸት "ቀጥሉ ግፉበት" የሚል ያልተጻፈ መልዕክት ለማንበብ ከሞከሩ ለእነሱ ለራሳቸውም ሆነ ለሃገራችን ብዙ ችግሮችን የሚያመጡ ታሪካዊ ስህተቶችን እየፈጸሙ እንደሆነ መገንዘብ አለባቸው::